11 ኛ ዓመት ቁጥር 19
11th Year No. 19

ባህር ዳር ሰኔ 8 ቀን 1998 ዓ.ም
Bahir Dar June 15, 2006

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ
የአማራ ብሔራዊ ክልል ምክር ቤት

# ዝክረ ሕግ
# ZIKRE HIG

## Of the Council of the Amhara National Regional State

ማውጫ

አዋጅ ቁጥር **134/1998** ዓ.ም
በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የኅብረት
ስራ ማህበራት ማቋቋሚያ አዋጅ

## in the Federal Democratic Republic of Ethiopia

በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ
መንግስት ምክር ቤት ጠባቂነት
የወጣ

✉ 1324
ያንዱ ዋጋ ብር 9.38
Unit price ------

አዋጅ ቁጥር **134/1998** ዓ.ም

በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የኅብረት ስራ ማህበራት ለማቋቋም የወጣ አዋጅ

**የህብረት ስራ ማህበራት በህብረተሰቡ ውስጥ የተበታተነውን የፋይናንስ፣የማቴሪያልና የሰው ሃይል ሃብት በማሰባሰብና በማንቀሳቀስ ከፍተኛ ልማት የሚፈጥሩ ተቋማት መሆናቸው በመታመኑ፤**



**መንግስት ያወጣቸውን የተለያዩ የልማት ፖሊሲዎችና ስትራቴጅዎች**

በመፈጸም ሂደት የህብረት ስራ ማህበራት ከፍተና ሚና ሊጫወቱ የሚችሉ መሆኑ አሳማኝ ሆኖ በመገኘቱ፤

አባላት የሚፈልጉት ግብአትና የኢንዱስትሪ ውጤት በተመጣጣኝ ዋጋ እንዲቀርብላቸውና የምርት ውጤታቸውም ሆነ አግልግሎታቸው በሃገር ውስጥና በውጭ ሃገር የተሻለ ዋጋ እንዲያገኝላቸው ለማድረግ የህብረት ስራ ማህበራት ሚና ተተኪ የሌለው በመሆኑ፤

በአጠቃላይ የህብረት ስራ ማህበራት በነጻ ገበያው ሥርዓት ውስጥ ተገቢውን ሚና እንዲጫወቱ ማድረግ በማስፈለጉ፤

ይህንን አላማ ለማሳካት የኅብረት ስራ ማህበራት የሚደራጁበትንና የሚተዳደሩበትን የተሟላ ህግ ማውጣት በማስፈለጉ፤

በተሻሻለው የብሔራዊ ክልሉ ህገ መንግስት አንቀጽ 49 ንዑስ አንቀጽ 3(1) ድንጋጌ መሰረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ ድንጋጌዎች

**1.** አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ የህብረት ሥራ ማህበራት አዋጅ ቁጥር 134/1998 ዓ.ም ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

**2.** ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፥-

1. "ማህበር" ማለት በዚህ አዋጅ መሰረት የተደራጀና የተመዘገበ የኅብረት ስራ ማህበር ሲሆን በተለይም ከዚህ በታች የተዘረዘሩትንና የመሳሰሉትን ይጨምራል፥-

   ሀ. የገበሬዎች የህብረት ስራ ማህበራት፤

   ለ. የመኖሪያ ቤት የህብረት ሥራ ማህበራት፤

   ሐ. የኢንዱስትሪና የእደ ጥበብ የህብረት ስራ ማህበራት፤

   መ. የሸማቾች ህብረት ስራ ማህበር፤

   ሠ. የገንዘብ ቁጠባና ብድር ኅብረት ስራ ማህበራት፤

   ረ. የዓሳ አስጋሪዎች የኅብረት ስራ ማህበራት፤

   ሰ. የማዕድን የኅብረት ስራ ማህበራት

2. "የኅብረት ስራ ማህበር" ማለት ሰዎች በፈቃደኝነት ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ችግሮቻቸውን በጋራ ለመፍታት የሚያቋቁሙትና ዲሞክራሲያዊ በሆነ መንገድ የሚስተዳድሩት ድርጅት ነው።

1. “ገቢ” ማለት የጤና ተቋማት ከሚሰጧቸው ማናቸውም የጤና አገልግሎቶችና ከሚያካሂዱት የመድሃኒትም ሆነ ሌሎች ዕቃዎች ሽያጭ የሚሰበሰቡት ገቢና በዓይነትም ሆነ በጥሬ ገንዘብ የሚያገኙት እርዳታ ነው፡፡
2. “የጤና መድን” ማለት የጤና አገልግሎት ተጠቃሚዎችን ወጪ ለመሸፈን የሚሰጥ ዋስትና ነው፡፡
3. “ቢሮ” ማለት የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የጤና ጥበቃ ቢሮ ነው፡፡
4. “ወረርሽኝ“ ማለት በዓለም አቀፍ ደረጃ ከተወሰነው መስፍርት ጣሪያ ባለፈ አኳኋን በአንድ የበሽታ አይነት የተጠቁ ሰዎች ቁጥራቸው በዝቶ የሚታይበት ክስተት ነው፡፡
5. “የመጣሻ ክፍያ“ ማለት አንድ ሰው በመሠረታዊ ጤና አገልግሎት ተቋም ሊያገኘው የሚችለውንና የሚገባውን አገልግሎት ደረጃው ከዚህ በላይ በሆነ ተቋም ለማግኘት ሲጠይቅ እንዲከፍል የሚጠየቀው ተጨማሪ ክፍያ ነው፡፡
6. “የአስቸኳይ ጊዜ የጤና አገልግሎት“ ማለት በተፈጥሮ ወይም በሰው ሰራሽ ክስተቶች ምክንያት ሕዝብ ለተላላፊ በሽታዎች ሲጋለጥ የሚሰጥ የጤና አገልግሎት ነው ፡፡
7. “ወጪን የሚሸፍን አካል “ማለት የመክፍል አቅም ለሌላቸው የኅብረተሰብ ክፍሎች የሚወጣውን የጤና አገልግሎት ወጪ በጀት በቅድሚያ ይዞ ለመሸፈን የሚስማማ ማናቸውም አካል ነው፡፡
8. “የግል የጤና ተቋም“ ማለት በጤናው ዘርፍ ከመንግሥት መዋቅር ውጭ በግልና መንግሥታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች አማካኝነት የጤና አገልግሎት እንዲሰጡ የተፈቀደላቸውን ድርጅቶች የሚያጠቃልል ነው ፡፡
9. የግል ሕክምና መስጫ ክፍል ውጭ የሆስፒታሉ አንድ አካል ሆኖ የሚቋቋምና ለተመላላሽ ወይም ተኝተው ለሚታከሙ በሽተኞች የሕክምና አገልግሎት የሚሰጥበት ክፍል ነው፡፡

10. "የቅብብሎሽ ሥርዓት" ማለት ከጤና ኬላ እስከ ልዩ ሆስፒታል ባለው የጤና ተቋማት አደረጃጃት ውስጥ በየደረጃዉ ለበሽተኞች የሚሰጠው የሕክምናና የጤና አጠባበቅ አገልግሎት ከአቅም በላይ ሆኖ ሲገኝ ለተሻለ አገልግሎት ከፍ ወዳሉት ተቋማት የማስተላለፍ የመቀበል አሰራር ነው ።

11. "ድንገተኛ "ማለት እንደ እራስ መሣት፤ የማያቋርጥ የደም መፍሰስ፤ የእሣት መቃጠል፤ በተለያዩ አራዊት መጠቃትና በመሳሰሉት አደጋዎች ምክንያት ቅጽበታዊ እርዳታ የሚያሻዉ ያልተጠበቀና የከፋ የጤና መታወክ ነው።

12. "ቤተሰብ" ማለት ባል፤ ሚስት፤ እናት፤ አባት፤ ልጅ፤

ውንድም፤ እህት ወይም በሕግ የታወቀ አሳዳጊና የሚያካትት ሲሆን በዚሁ ተቋም ውስጥ የሚተዳደሩ ሌሎች አባላትን ይጨምራል።

13. “ሰው ማለት ማንኛውም የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው ።

## 1. <u>ዓላማዎች</u>

<u>አዋጁ የሚከተሉት አላማዎች ይኖሩታል፡-</u>

1. በሽታዎችን በመከላከልና በመሠረተ ጤና አገልግሎት መስፋፋት ላይ ያተኮረውን የሀገሪቱን የጤና ፖሊሲ በክልሉ ውስጥ በአግባቡ ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችል የሕግ ማዕቀፍ ማደራጀት፤
2. የጤና አገልግሎቱን ለሕብረተሰቡ በዘላቂነት መስጠት ይቻል ዘንድ የጤናው ዘርፍ በቂ ሀብት የሚያገኝበት ምቹ ሁኔታ መፍጠር፤
3. የአገልግሎቱን ሽፋን ለማሣደግና ጥራቱን ለመጠበቅ ይቻል ዘንድ የመንግሥትም ሆኑ የግሉ ሴክተር ጤና ተቋማት መንግሥታዎ ካልሆኑ ድርጅቶችና ከሕብረተሰቡ ጋር ተቀናጅተው የሚሰሩበትን ሁኔታ ማመቻቸት፤

**4.** <u>የጤና አገልግሎት አሠጣጥ መርሆዎች</u>

1. የጤና ተቋማት የሚሰጡት ማናቸውም የጤና አገልግሎት ተመጣጣኝ ክፍያ የሚጠየቅበት ይሆናል። የአገልግሎቱ አይነትና የክፍያው መጠን በቢሮው ተጠንቶ በደንብ ይወሰናል።
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቅጽ **1** ስር የተደነገገው ቢኖርም ማናቸውም ሰው የሚከፍለው በማጣቱ ምክንያት ከመንግሥት ጤና ተቋማት የጤና አገልግሎት ከማግኘት አይከለከልም።
3. አግባብ ያላቸው የመንግሥት አካላት በሚሰጡት የነጻ የሕክምና ማስረጃ መሠረት ማንኛውም ሰው ነፃ የሕክምና አገልግሎት ሊያገኝ ይችላል፤ ዝርዝሩ በደንብ ይወሰናል።
4. የጤና ተቋማት በዕቅድ ዝግጅትና በጤና አገልግሎት አሰጣጥ ጉዳይ የሕብረተሰቡን ተሣትፎ ማረጋገጥ አለባቸው።
5. የመንግሥት የጤና ተቋማት አሠራር በሀብት አጠቃቀም ረገድ ወጭ ቆጣቢ፤ ግልጽነትንና ተጠያቂነትን የተላበሰ እንዲሁም ውጤትን የሚያስመዘግብ መሆን አለበት ።
6. ማንኛውም የጤና ተቋም ቅድመ ክፍያ ሳይጠይቅ ድንገተኛ የጤና አገልግሎት የመስጠት ግዴታ አለበት ።

<u>ክፍል ሁለት</u>

<u>የጤና አገልግሎት አሰጣጥ</u>

5. <u>የሕዝብ ጤና አጠባበቅ፤</u>

የሕዝብ ጤና አጠባበቅ፤ የአካባቢ ደህንነት፤ የምግብና የመጠጥ ውሃ ንጽሕና፤ የቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ፤

የተላላፊ በሽታዎች ክትትልና ቁጥጥር፤ የሥራ ነክ ጤና አጠባበቅ፤ በጤና ላይ ጉዳት ሊያስከትሉ የሚችሉ መሣሪያዎች አጠቃቀም እና ተያያዥነት ያላቸዉ ተግባራት አፍጻጸም የሚመራው ስለነዚሁ ጉዳዩች በተለይ በወጣው የሃይጅንና የአካባቢ ጤና አጠባበቅ ደንብ መሠረት ይሆናል።



## 6. <u>የእናቶችና ሕጻናት ጤንነት</u>

1. እናቶች ከእርግዝና በፊትና በእርግዝና ወቅት እንዲሁም በወልድ እና ድኀረ ወሊድ ጊዜያት የጤና አገልግሎት እንዲያገኙና ጤናቸው እንዲጠበቅ ቢሮው ሁኔታዎችን

ያመቻቻል።

2. ቢሮው የሕጻናትን ጤንነትና ዕድገት ለማረጋገጥ በየዕድሜ ደረጃቸው የሚያጋጥሟቸውን የጤና ችግሮች በመለየት አስፈላጊውን የጤና አገልግሎት የሚያገኙበትን ምቹ ሁኔታ ይፈጥራል።
3. የሕጻናትን ገዳይ በሽታዎች ለመቆጣጠር ለሁሉም ሕጻሃትን ገዳይ በሽታዎች ለመቆጣጠር ለሁሉም ሕጻናት ክትባት በነጻ እንዲሰጥ ይደረጋል።

**7.** <u>የአካል ክፍልን ወይም ደምን ስለመለገስ</u>

1. ማንኛውም ሰው በ 1952 ቱ ዓ.ም የፍትሃ ብሄር ሕግና በዚህ አዋጅ መሠረት በሕይወት ሣለም ሆነ ከሞት በኋላ የአካሉን ክፍል ወይም ደሙን ለሕክምና አገልግሎት እንዲውል በሙሉ ፍላጎት መለገስ ይችላል። አስቀድሞ ፈቃዱን ሳይሰጥ ከሞተ ከማንኛውም ሰው አስክሬን ማናቸውንም የአካል ክፍል ለሕክምና አገልግሎት መውሰድ የሚቻለው የሚቹ ቤተሰቦች ስለጉዳዩ ተጠይቀው በጽሁፍ ሲስማሙ ብቻ ይሆናል።

2. ዝርዝር አፈጻጸሙ በደንብ ይወሰናል።

**8.** የአስከሬን ምርመራ ስለማድረግና የሞት ማስረጃ ስለመስጠት

1. ለሕክምናና ለሕግ ጉዳዩች የሚችን የሞት መንስኤ ለመለየት ወይም ለማረጋገጥ ሲባል የአስከሬን ምርመራ ማድረግ ይቻላል።
2. ለሞተ ሰው የሞቱን መንስኤ በሚመለከት ማንኛውም አካል ሲጠይቅ የጤና ተቋማት መርምረው ተገቢውን የጽሁጽ ማስረጃ የመስጠት ግዴታ አለባቸው።

1.

3. የአስከሬን ምርመራ የሚካሄድበትና የሞት ማስረጃ የሚሰጥበት ዝርዝር የአሠራር ሥርዓት በደንብ ይወሰናል ፡፡

## 9. የታካሚዎችን ፈቃድ ስለማግኘት

1. ሕግ በሌላ አኳኋን እንዲፈጸም ካላስገደደ በስተቀር ማንኛውም የሕክምና አገልግሎት የሚሰጠው በፍትሃብሔር ሕግ ቁጠር 20 እና በዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች መሠረት በታካሚው ፈቃድ ይሆናል፡፡
2. ፈቃድ መስጠት የማይችሉ ታካሚዎች እርዳታ የሚከናወነው ስለዝሁ ጉዳይ በተወሰነው ሕግ ወይም በታወቀ አሠራር መሠረት ይሆናል፡፡

## 10. ፈቃድ ስለማግኘት

1. ማንኛውም የጤና ባለሙያ በጤና አገልግሎት ሥራ ላይ ለመሠማራት በቅድሚያ የሙያ ምዝገባና የሥራ ፈቃድ ሊኖረው ይገባል፡፡
2. የፌዴራሉ መንግሥት ሕግጋት እንደተጠበቁ ሆነው በጤና አገልግሎት መስክ ለመሠማራት የሚፈልግ ማናቸውም መስክ ለመሠማራት የሚፈልግ ማናቸውም ሰው በቅድሚያ ከቢሮው ፈቃድ ማግኘት አለበት ፡፡

## 11. የጤና ባለሙያዎች የሙያ ኃላፊነት

ማንኛውም የጤና ባለሙያ በሙያውና በደረጃው አንጻር ከዚህ በታች የተመለከቱት ግዴታዎች ይኖሩታል ፡-

1. የሕብረተሰቡን ጤና የመጠበቅና የመንከባከብ፤
2. የጤና አጠባበቅ ትምህርት የመስጠት፤
3. በሳይንሳዊ ምርምሮች የመሳተፍ፤ የበታች የጤና ባለሙያዎችን የማስተማርና ራሱንም በትምህርት የማጎልበት፡፡

## 12. <u>የሙያ ሥነ ምግባር</u>

ማንኛሙም የጤና ባለሙያ ብሮው የሚያወጣውን የሥነ ምግባር መመሪያ የማክበር ግዴታ አለበት፡፡



## 13. <u>ስለ ሕክምና አሰጣጥ ቅብብሎሽ ሥርዓት</u>

1. ማንኛውም የጤና ባለሙያ ወይም ተቋም በደረጃው የሚጠበቅበትን የጤና አገልግሎት መስጠት አለበት፡፡
2. ሕሙማን ከአንድ ጤና ተቋም ወደ ሌላ ጤና ተቋም

የሚላኩት ለዚሁ የሚሰራበትን የቅብብሎሽ ሥርዓት በተከተለ መንገድ ይሆናል።

3. ሕሙማን የቅብብሎሽ ሥርዓቱን ሣይከተሉ የጤና አገልግሎት ለማግኘት ቢፈልጉ የመጣሻ ክፍያ እንዲከፍሉ ይደረጋል፡

**14.** ስለግል የሕክምና መስጫ ክፍሎች

1. የመንግሥት ጤና ተቋማት እንደሆኔታው ከመደበኛው አገልግሎታቸው ጎን ለጎን ለተመላላሽ እና ወይም ተኝተው ለሚታከሙ ሕሙማን ተጨማሪ ክፍያ በማስከፈል የሕክምና አገልግሎት የሚሰጡ የግል ሕክምና መስጫ ክፍሎች ሊያቋቁሙ ይችላሉ።
2. በመንግሥት የጤና ተቋማት ውስጥ የሚደራጁት የግል የሕክምና መስጫ ክፍሎች አመራር፤ አስተዳደርና አሠራር ተጠንቶ በደንብ ይወሰናል።

**15.** አገልግሎቶችን በውል ስለመስጠት

**1.** የመንግሥት ጤና ተቋማት ሕክምና ነክ ያልሆኑ አገልግሎቶች እንደሆኔታው ብቃት ያለው አገልግሎት መስጠት

ለሚችሉ አካላት በውል መስጠት ይችላሉ

**2.** የመንግሥት ጤና ተቋማት አገልግሎቶችና በውል የሚሰጡበት ዝርዝር ሁኔታ በደንብ ይወሰናል ።።

**16.** የመረጃ አያያዝና አጠቃቀም

1. ቢሮው በኀብረተሰቡ የጤና ሁኔታና የአገልግሎት አሰጣጥ ላይ ያተኮረ ወቅታዊ መረጃ የሚያዝበትንና ጥቅም ላይ የሚውልበትን ሁኔታ ያመቻቻል ።
2. ማንኛውም የጤና ተቋም የሚሰጠውን አገልግሎት በሚመለከት ወቅታዊ መረጃ የመያዝ፤ የማደራጀትና አስፈላጊ ሲሆን አግባብ ላላቸው አካላት የማስተላለፍ ግዴታ አለበት

## ክፍል ሦስት

## የአስቸኳይ ጊዜ የጤና አገልግሎትና የድንገተኛ አደጋ ሕክምና

### 17. የአስቸኳይ ጊዜ የጤና አገልግሎት

1. ቢሮው በወረርሽኝ መልክ የሚከሰቱ የበሽታ ዓይነቶችን ይለያል፤ ተገቢውን መረጃ ያሰባስባል፤ በወቅቱና ቀጣይነት ባለው አኳኋን ለሚመለከታቸው ሁሉ ያሰራጫል።
2. ቢሮው የጤና አገልግሎት የአመራር አካላትና የጤና ተቋማት አደጋ ከመድረሱ በፊት ለመከላከልና ለመቆጣጠር የሚያስችሉ የመጠባበቂያ ግብዓቶች እንዲሟሉላቸውና የመረጃም ሆነ የሎጀስቲክስ አቅም እንዲገነቡ ያደርጋል።
3. ቢሮው የሕብረተሰቡን ንቁ ተሳትፎ በማረጋገጥ እና ከሌሎች የአስቸኳይ ጊዜ እርምጃ ከሚወሰዱ አካላት ጋር በመቀናጀት የአስቸኳይ ጊዜ የጤና አገልግሎትን ያደራጃል፤ ያስተባብራል፤ ያስፈጽማል፤ ክትትል ያደርጋል።
4. ማንኛውም የጤና ተቋም በወረርሽኝ እና ሌሎች አስቸኳይ

የጤና አገልግሎት ሥራዎች ላይ የመሳተፍና የመተባበር ግዴታ አለበት ፡፡

5. ማንኛውም የጤና ተቋም ቅድመ ክፍያ ሳይጠይቅ የአስቸኳይ ጊዜ የጤና አገልግሎት የመስጠት ግዴታ አለበት ፡፡

6. የአስቸኳይ ጊዜ የጤና አገልግሎት የአሠራር

7. ሥርዓት ቢሮው በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል ፤

**18.** <u>የድንገተኛ አደጋ ሕክምና አገልግሎት</u>

1. ማንኛውም የጤና አገልግሎት መስጫ ተቋም የድንገተኛ አደጋ ሕክምና መስጫ ክፍል ማደራጀት አለበት ፡፡
2. በየትኛውም የጤና ተቋም ውስጥ የሚገኝ የድንገተኛ አደጋ ሕክምና አገልግሎት መስጫ ክፍል አገልግሎቱን በቀንም ሆነ በማታ የመስጠት ግዴታ አለበት ፡፡

3. ማንኛውም የጤና ተቋም በድንገተኝነት ለሚቀበላቸው ሕሙማን የመጀመሪያ ደረጃ ሕክምና መስጠትና ታካሚው ወይም ተጎጂው ቀጣይ የሕክምና አገልግሎት እንዲያገኝ ሁኔታዎችን ማመቻቸት ይኖርበታል።

4. የድንገተኛ አደጋ ሕክምና አገልግሎት አደጋው በተከሰተበት ሥፍራ ቄምር የሚሰጥባቸውንና ሕብረተሰቡ ትምህርት የሚያገኝባቸውን ሁኔታዎች ቢሮው ያመቻቻል።

5. ማንኛውም የሕክምና ባለሙያ በማናቸውም ጊዜና ሁኔታ የድንገተኛ አደጋ ሕክምና አገልግሎት የመስጠት ግዴታ አለበት ።

## ክፍል አራት

## ስለጤና አገልግሎት አደረጃጀትና አስተዳደር

### 19. ስለክልሉ ጤና አገልግሎት አደረጃጀትና አስተዳደር አመራር

የክልሉ መንግሥት ለሕብረተሰቡ የሚያቀርበው የጤና አገልግሎት የሚደራጀውና የሚመራው ከዚህ በታች በተመለከቱት አካላት ይሆናል፡-

ሀ. ቢሮ

ለ. የሆስፒታሎች ሥራ አመራር ቦርድ

ሐ. የሆስፒታል ሥራ አስኪያጅ / ሥራ አስኪያጆች

መ የወረዳ ጤና ጥበቃ ጽ/ቤት

ሠ.የመሠረታዊ ጤና አገልግሎት ሥራ አመራር ኮሚቴ

ረ. የመማክርት ጉባኤ

### 20. ስለቢሮው ልዩ ስልጣን

የብሔራዊ ክልላዊ መንግስቱን አስፈጻሚ አካላት እንደገና ለማደራጀትና

ስልጣንና ተግባራቸውን ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 60/1994 ዓ.ም/ እንደተሻሻለ/ አንቀጽ 16 ሥር የተሰጡት ጠቅላላ ስልጣንና ተግባራት እንደተጠበቁ ሆነው ቢሮው ከዚህ በታች የተመለከተው ልዩ ስልጣን ይኖረዋል፡-



1. ሃገራዊ ተቀባይነት ያላቸውን መስፈርቶች ግመምት ውስጥ በማስገባት የጤና ተቋማት ሊኖራቸው የሚገባውን የሰው ኃይል

ብዛት፣ ብቃትና ስብጥር እንዲሁም የሕንጻ፣ የሕክምና መሣሪያዎችና መገልገያዎች ደረጃ ይወስናል፣

2. የተገልጋዩን ሕብረተሰብ የመክፈል አቅምና የተቋማቱን ወጪ በማመዛዘን የጤና ተቋማቱ በሚያቀርቡት ሃሣብ መሠረት የመንግሥት ጤና ተቋማት ለሚሠጡት የጤና አገልግሎት ሊፈጸም የሚገባውን ክፍያ መጠን የሚወሰን መመሪያ ያወጣል፤ በተግባር ላይ እንዲውል ያደርጋል፤

3. የጤና ተቋማቱ የሰው ኃይል ብቃት፤ የአሠራር ሥርዓትና ድርጅታዊ አቅም እንዲጠናከር ተገቢውን እገዛ ያደርጋል፤

4. የጤና ድርጅቶችን ደረጃ ለመለየት የሚያስችል መመዘኛ ያወጣል፤ በዚህ መሠረት ለጤና አገልግሎት መስጫ ተቋማት ደረጃ ይሰጣል፤

5. በክልሉ ውስጥ የሚገኙ የግል፤ የመንግስትና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ንብረት የሆኑ የጤና አገልግሎት መስጫ ተቋማት ለህብረተሰቡ ደረጃውን የጠበቀ አገልግሎት ለማስፋፋትና ጥራቱን ለማሻሻል የወጡ ለዩ ልዩ ደንቦች፤ መመሪያዎችና መሥፍርቶች ተከብረው በሥራ ላይ መዋላቸውን ይከታተላል፤ ይቆጣጠራል፤

6. አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ስልጣኑን አግባብ ላለው አካል በውክልና ሊያስተላልፍ ይችላል፤

7. ቢሮው በማናቸውም የጤና አገልግሎት መስጫ

ተቋም የሚሰሩ ባለሙያዎች ሙያው የሚጠይቀውን የሥነ ምግባር ደረጃ ጠብቀው ሥራቸውን ማከናወናቸውናንና ተቋማቱም ይህንኑ ማስከበራቸውን በየጊዜው ይከታተላል፤ ይቆጣጠራል።

**21.** የሆስፒታሎች ሥራ አመራር ቦርድ

1. ማናቸውም የክልሉ መንግሥት ሆስፒታል ሕጋዊ ሰውነትያለውና ራሱን የቻለ ሆኖ ይደራጃል፤ በራሱ የሥራ አመራር ቦርድና ሥራ አስኪያጅ /ሥራ አስኪያጆች/ ይመራል፤ ይተዳደራል ፡፡
2. የየሆስፒታሉ ስራ አመራር ቦርድና ስራ አስኪያጆች ዝርዝር የስራ ድርሻና ኃላፊነት በደንብ ይወሰናል ፡፡

**22.** <u>የሆስፒታሎች ስልጣንና ተግባር</u>

እያንዳንዱ ሆስፒታል በዚህ አዋጅ መሠረት የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1. በሽታዎችን በመከላከልና በመቆጣጠር ላይ አተኩሮ ለሕሙማን ደረጃውን የጠበቀ የሕክምና አገልግሎት ያቀርባል፤
2. በውስጡ የሚገኙ ሙያተኞችና ድጋፍ ሰጭ ሠራተኞች ተገቢውን ሥልጠና እንዲያገኙ ያደርጋል፤
3. የንብረት ባለቤት ይሆናል፤ ውል ይዋዋላል፤ በስሙ ይከሳል፤ ይከሰሳል፤
4. የባንክ ሂሣብ በስሙ ይከፍታል፤ ያንቀሳቅሳል፤
5. ሃብቱን በልማት ላይ ያውላል።

## 23. ስለወረዳ ጤና ጥበቃ ጽ/ቤት

የወረዳ ጤና ጥበቃ ጽ/ቤት በተደራጀበት አካባቢ የሚኙትን የጤና ተቋማት አስመልክቶ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 20 ድንጋጌዎች ለቢሮው የተሰጠውን ስልጣንና ተግባራት እንደአግባብነታቸው በሥራ ላይ ያውላል።

## 24. የመሠረታዊ ጤና አገልግሎት ሥራ አመራር ኮሚቴ

1. የመሠረታዊ ጤና አገልግሎት ተቋማት አመራር ኮሚቴ ከተገልጋዩ ሕብረተሰብና ከሚመለከተው ጤና ተቋም በተውጣጡ ጥምር አባላት የሚዋቀር ይሆናል።
2. ዝርዝር የሠራ ድርሻው ይህንን አዋጅ መሠረት አድርጎ ቢሮው በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል ።

**25.** <u>የመማክርት ጉባኤ</u>

1. የክልሉ የጤና ተቋማት የጤና አገልግሎት ሽፋንና ጥራት እንዲሻሻል በሚደረገው ጥረት በሁለገብ አማካሪነት የሚያገለግል የመማክርት ጉባኤ ይቋቋማል፡፡
2. የጉባዔው አባላት በቢሮው የሚሰየሙ ሲሆን፣ ዝርዝር ተግባርና ኃላፊነታቸው በመመሪያ ይወሰናል፡፡

<u>ክፍል አምስት</u>

<u>ስለመንግሥት የጤና ተቋማት ፋይናንስ</u>

**26.** <u>የጤና ተቋማት የፋይናንስ ምንጭ</u>

1. በክልሉ መንግሥት የሚመደብ ጥቅል በጀት፤
2. ተቋማቱ ከሚሰጡት የጤና አገልግሎት የሚሰበሰብ ገቢ፤
3. ከለጋሽ ድርጅቶችና ግለሰቦች የሚሰጥ የአይነትና የጥሬ ገንዘብ ስጦታ ወይም እርዳታ፤
4. ሌሎች፡፡

**27.** <u>በገቢ ስለመጠቀም</u>

1. በክልሉ ውስጥ የሚገኙ ሆስፒታሎችና ጤና ጣቢያዎች በመንግሥት ተወስኖ ከተመደበላቸው ውጭ የሚያገኙት ማናቸውም ገቢ በጤና ተቋማቱ ስም በተከፈተ ልዩ የባንክ

ሂሣብ ውስጥ ይቀመጣል፡፡

2. ሆስፒታሎችና ጤና ጣቢያዎች ከክልሉ መንግሥት በጥቅል ከሚመደብላቸው በጀት በተጨማሪ ከሚሰጡት አገልግሎት የሚያገኙትን ገቢ ሙሉ በሙሉ ለሥራዎቻቸው ማስፈጸሚያ ያውላሉ፡፡
3. የሆስፒታሎችና ጤና ጣቢያዎች ገቢ አሰባስብና አጠቃቀም ሥልጣን በተሰጠው የመንግሥት አካል በየጊዜው ኦዲት ይደረጋል፡፡
4. የጤና ተቋማት የውስጥ ገቢ አሰባሰብና አጠቃቀም ዝርዝር ቢሮው ከክልሉ ገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ ጋር በመመካከር በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል ፡፡

**28.** የጤና አገልግሎት ክፍያ

በክልሉ የጤና ተቋማት ሊፈጸም የሚገባው የአገልግሎት ክፍያ መጠን ቢሮው አጥንቶ በሚያቀርበው ሀሳብ ላይ ተመስርቶ በክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት የሚወሰንና በስራ ላይ የሚውል ይሆናል።

**29.** የጤና መድህን ስለማቋቋም

1. ቢሮው የጤና መድህን ዋስትና ለማቋቋምና ለማስፋፋት የሚረዱ አመቺ ሁኔታዎችን ይፈጥራል።
2. የጤና መድህን ዋስትና የሚከተሉትን የአደረጃጀት ዓይነቶች መሠረት በማድረግ ሊቋቋም ይችላል፡-
   ሀ. የግል የጤና ተቋማት የሚዘረጉት የጤና መድህን ሥርዓት ፤
   ለ. የተለያዩ የማኅበረሰብ ተቋማት የሚዘረጉት የጤና መድህን ሥርዓት ፤
   ሐ. አሠሪዎች ለሠራተኞቻቸው የጤና መድህን ፖሊሲዎችን እንዲገዙና በራሳቸው የመድህን ሽፋን እንዲያቋቁሙ ማድረግ ፤
   መ. መንግሥት ለሠራተኞች ማህበራዊ የጤና መድህን ፖሊሲ የሚገዛበት ሁኔታ ፡

**30.** ስለዕቃና አገልግሎት ግዢ

ሆስፒታሎችና ጤና ጣቢያዎች የዕቃና አገልግሎት ግዥ የሚፈጽሙት አግባብ ያላቸውን የክልሉን መንግሥት የዕቃና አገልግሎት ግዥ መመሪያዎች በመከተል ይሆናል፡፡



ክፍል ስድስት

ስለነጻ ሕክምናና ክፍያ ስለማይጠይቅባቸው የጤና አገልግሎቶች

**31.** የነጻ ሕክምና አገልግሎት ተጠቃሚዎች

1. የመክፈል አቅም የሌላቸው ስለመሆኑ ተረጋግጦላቸው ነጻ የሕክምና ማስረጃ የሚያቀርቡና በዜግነት ኢትዩ É ያውያን የሆኑ የክልሉ ነዋሪዎች ከክልሉ መንግሥት የጤና

አገልግሎት መስጫ ተቋማት ነጻ የሕክምና አገልግሎት ያገኛሉ፤

2. የነጻ ሕክምና ማስረጃ የሚሰጥ ማንኛውም አካል ለአገልግሎቱ የሚወጣውን ወጪ የመሸፈን ኃላፊነት ይኖርበታል፤

3. ነጻ የሕክምና አገልግሎት የሚሰጣቸዉ ተጠቃሚዎች የሚለዩበትና የወጪው አሸፋፈን አግባብ ይህንኑ አስመልክቶ በሚወጣ ደንብ ይወሰናል።

**32.** <u>ክፍያ ስለማይጠየቅባቸው የጤና አገልግሎቶች</u>

1. በክልሉ ውስጥ የሚገኙና የመንግሥት የሆኑ የጤና ተቋማት ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን የጤና አገልግሎቶች በዚህ አዋጅ መሠረት ያለክፍያ ይሰጣሉ፡-

ሀ. ከሣንባ ነቀርሣ በሽታ ጋር በተያያዘ የአክታ ምርመራ ፤ ክትትልና የመድኃኒት አቅርቦት፤

ለ. በመሠረታዊ የጤና አገልግሎት መስጫ ተቋማት አማካኝነት የሚሰጥ የቅድመ ወሊድ፤የወሊድ፤የድህረ ወሊድና የቤተሰብ

ምጣኔ አገልግሎት፤

ሐ. የክትባት አገልግሎት፤

መ. በፈቃደኝነት ላይ የተመሠረተ የኤች .አይ. ቪ/ኤድስ ምርመራ፤

ሠ. ኤች. አይ. ቪ/ኤድስ ከእናት ወደ ጽንስ እንዳይተላለፍ የሚሠጥ የመከላከል አገልግሎት፤

ረ. ስጋ ደዌ

ሰ. ፊስቱላ፤

ሸ. ወረርሽኝ፤

ቀ.ወጪያቸው በመንግሥት የሚሸፈን ሆኖ ወደፊት ያለክፍያ እንዲሰጡ በክልሉ መስተዳደር ም/ቤት የሚወሰኑ ሌሎች የጤና አገልግሎቶች።

2. ክፍያ የማይጠየቅባቸውን የጤና አገልግሎቶች የሚሰጥ ማንኛውም የጤና ተቋም የዚህ አይነቶቹን አገልግሎቶች የሚያሣይ መረጃ ለይቶ እና አደራጅቶ በመያዝ ለቢሮው የማሣወቅ ግዴታ አለበት።

## ክፍል ሰባት

## የመንግሥት፤መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችና የግሉ ዘርፍ ቅንጅት

**33.** <u>*የሥራ አካባቢን ስለማሻሻልና ድጋፍ ስለማድረግ*</u>

1. ቢሮው የሙያ ሥነ-ምግባት በማስፈን፤ በፖሊሲ ነክ ጉዳዮች፤ በቴክኒክና በአሠራር ነክ የማሻሻያ ሥራዎች ከግሉ ዘርፍ የጤና ተቋማት ጋር በቅንጅት ይሠራል።
2. በክልሉ ውስጥ የጤና ተቋማት እንዲስፋፉና የአገልግሎታቸው ጥራት እንዲሻሻል ቢሮው ለግልና ለሌሎች መንግሥታዊ ላልሆኑ ድርጅቶች አስፈላጊውን የቴክኒክ እገዛ ያደርጋል።

**34.** <u>*መረጃን ስለማጠናቀር*</u>

1. የግል ጤና ተቋማት የሚያደርጉትን ተሣትፎና የሚያጋጥማቸውን ችግር በአግባቡ መለየትና ተገቢውን እርምጃ መውሰድ እንዲቻል ቢሮው በግሉ የጤና ተቋማት ላይ ወቅታዊ የመረጃ ጥንቅር የሚኖርበትን ሁኔታ ያመቻቻል፤ ጥናቶችንም በቋሚነት ያካሂዳል።

2. የመንግሥትና የግሉ የጤና ተቋማት ቢሮው በሚያወጣው መመሪያ መሠረት ስለበሽታዎች አይነት እና ሥርጭት ወቅታዊ የሆነ የመረጃ ልውውጥ ማድረግ አለባቸው።
3. ማናቸውም የጤና ተቋም የሚሰጠውን አገልግሎት በማመለከት ዕለታዊና ተዓማኒነት ያለው መረጃ የመያዝ ግዴታ አለበት።

## ክፍል ስምንት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

**35.** ተፈጻሚነት ስለማይኖራቸው ሕጎች

ይህንን አዋጅ የሚቃረን ማናቸውም ሕግ፤ ደንብ፤ መመሪያ ፤ ወይም የተለመደ አሠራር በዚህ አዋጅ ውስጥ በተመለከቱት ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት አይኖረውም ።

**36.** ደንብና መመሪያ የማውጣት ሥልጣን

1. የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት ለዚህ አዋጅ ሙሉ ተፈጻሚነት የሚያስፈልጉትን ደንቦች ሊያወጣ ይችላል ።
2. ቢሮው ለዚህ አዋጅና በአዋጅ መሠረት ለሚወጡ ደንቦች ተግባራዊነት የሚያስፈልጉትን ዝርዝር መመሪያዎች ሊያወጣ ይችላል።

**37.** አወጁ የሚጸናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ በክልሉ መንግሥት ዝክረ ሕግ ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል።

ባህር ዳር

ሐምሌ 20 ቀን 1997 ዓ.ም

ዮሴፍ ረታ

የአማራ ብሔራዊ ክልል

ፕሬዚዳንት